ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ጁማዳ አል አኺራህ 4/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስቴር ጃንዮሪ 7/2022 ግ.

# ሥራ ክብር ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَقُلِ اعْمَلُوا فَسَيَرَى اللَّهُ عَمَلَكُمْ وَرَسُولُهُ وَالْمُؤْمِنُونَ وَسَتُرَدُّونَ إِلَى عَالِمِ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ}

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(በላቸውም ሥሩ አላህ ሥራችሁን በእርግጥ ያያልና፡፡ መልክተኛውና ምእምናንም (እንደዚሁ ያያሉ)፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደ ኾነውም (አላህ) በእርግጥ ትመለሳላችሁ፡፡ ትሠሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

የእስልምና እምነት ሥራን የሚመለከተው በአክብሮትና በመቀደስም ጭምር ነው፡፡ እሱ የእድገትና የብልጽግና ጎዳና ነው፡፡ ቅዱስ ቁርአንን ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው ይህችን ዓለም ለማልማትና በዚህች ዓለም ደግ ነገር ሁሉ እንዲስፋፋ መነሻ ወደሆነው ሥራ በግልጽ የሚገፋፋ መሆኑን ሊረዳ ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ الأَرْضِ وَاسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا}

(እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፡፡ በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ፡፡) እንዲሁም እንድህ ይላል፡

{هُوَ الَّذِي جَعَلَ لَكُمُ الأَرْضَ ذَلُولًا فَامْشُوا فِي مَنَاكِبِهَا وَكُلُوا مِنْ رِزْقِهِ وَإِلَيْهِ النُّشُورُ}

(እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎችዋና በመንገዶችዋም ኺዱ፡፡፡ ከሲሳዩም ብሉ፡፡ (ኋላ) መመለሻውም ወደእርሱ ብቻ ነው፡፡) በሌላም አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِنْ فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيراً لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

(ሶለቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህንም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡)

ከስግደት ቀጠሎ የታዘዘንበት ተግባር መሆኑ የሥራን አስፈላጊነት በግልጽ ያሳያል፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዒራክ ኢብን ማሊክ የተሰኙት ሊቅ የአርብን ስግደት ከፈጸሙ በኋላ ከመስጊድ ይቆሙን እንድህ ይሉ ነበር፡ « ጌታየ ሆይ! እነሆ አኔ ጥሪህን ተቀብየ ግድ ያደረግህብኝን ስገዴት ፈጸመኩኝ አንዳዘዘከኝም ከተበታኞቹ ጋር ተበትኛለሁ፡፡ ከችሮታህም ስጠኝ፡፡ አንተ ከሰጭዎች ሁሉ በላጭ ነህና፡፡»

ንጹኃን ነብያዊ ፈለጎች የሰውን ልጅ የበላይነት የሚጠብቅና ክብር በመሆኑ ወደሥራ በመጋፋፋትና በሱም ታታሪ ወደመሆን የሚያዙ ምክሮች በሰፊው ይገኙባቸዋል፡፡

ነብያችን (ሶ.0.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ከሥራዎች በላጩ ከማታለል ነጻ የሆነ ንግድ እንድሁም እንድ ሰው በእጁ የሚያከናውነው ሥራ ነው፡፡) እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ ( አንዳችሁ በትከሻው አንድ ሸክም እንጨት ተሸክሞ ሸጦ ገንዘብ ማግኘቱ ሰጠውም ከለከለውም አንድን ሰው ከመለመኑ ይሻለዋል፡፡)

(አላህ ምህረቱን ይችራቸውና) ሱፍያን አሰውሪ የተባሉት ሊቅ አንድ ቀን በመስጂደልሐራም ውስጥ ሲይልፉ ሰዎች ተቀምጠው አገኙ፡፡ ‹‹ለምንድን ነው እዚህ የተቀመጣችሁት ሲሉም ጠየቁ፡፡ ሰዎቹም ምን እንሥራ ሲሉ መለሱ፡፡ እርሳቸውም የአላህን ችሮታ ፈለጉ፡፡ የሙስሊሞች ሸክም አትሁኑ፡፡» አሏቸው፡፡

(ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር አብንል ኸጣብ እንድህ ይሉ ነበር፡፡ ‹‹እንዳችሁ ጌታየ ሆይ! ሲሳይን ስጠኝ እያለ ሲሳይ መፈለጉን ትቶ አይቀመጥ፡፡ እናንተ ሰማይ ወርቅ ወይም ብር የማታዘምብ መሆኑን ታውቃላችሁና››፡፡

ሥራ ክብርና አጅግ አስፈላጊም በመሆኑ (በነሱ ላይ ሰላም ይውረድና) ነብያት በእጃቸው ሥራ ነበር የሚተዳደሩት፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይሉ ነበር፡ (በርሳቸው ሰላም ይውረድና) ነብዩ ዳውድ ከእጃቸው ሥራ እንጂ አይበለውም ነበር፡፡ ነብዩ ዘከርያም አናፂ ነበሩ)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የሚያስፈልጋቸውን ነገር በራሳቸው ያከናውኑ እንድሁም ቤተሰቦቻቻውን ያግዙ ነበር፡፡ (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) እናታችን ዓኢሻ እንድህ ይላሉ፡ ‹የአላህ መልክትኛ ጫማቸውን ይሰፉ ነበር እንድሁም ልብሳቸውን ይጠቅሙ ነበር››፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሕይወታችን ፍፃሜ ላይ ብንሆንም እንኳ ለሥራ ወደኋላ እንዳንል አዘውናል፡፡ እንድህም ይላሉ፡ (በእንዳችሁ እጅ የሚተከል ፍል እያለ የትንሳኤ ቀን ቢደርስና ከመነሳቱ በፊት እሱን መተከል የሚችል ከሆነ ይትከለው)፡፡

የሥራ ክብርነት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ የእስልምና እምነት አንድ ሰው የእለት ምግቡንና የልጆቹን ቀለብ ለማሟላት ሲጥር ጉዳት ቢደርስበት ሰማእት መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ቅዱስ ቁርኣን ከሥራና እውነትን የበላይ ለማድረግ ከሚደረገው መስዋእትነት መካከል ያለው ትስስር እንድህ በማለት ገልጾታል፡

{ وَآخَرُونَ يَضْرِبُونَ فِي الْأَرْضِ يَبْتَغُونَ مِن فَضْلِ اللَّهِ وَآخَرُونَ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ }

(ሌሎችም ከአላህ ችሮታ ለመፈለግ በምድር ላይ የሚጓዙ፣ ሌሎችም በአላህ መንገድ (ሃይማኖት) የሚጋደሉ እንደሚኖሩ (ዐወቀ)፡፡) ከእለታት አንድ ቀን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከባልደረቦቻቸው ጋር በተቀመጡበት ቦታ አጠገብ አንድ ሰውዬ አለፈ፡፡ ባልደረቦቻቸውም ብርታቱና ታታሪነቱ እጅግ ደነቃቸውና ይህ ብርታቱና ታታሪነቱ በአላህ መንገድ ቢውል እዴት ደግ ነበር አሉ፡፡ ያን ጊዜ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ አሉ፡ (ለህፃናት ልጆቹ ፍላጎት ለማሟላት የሚጥር ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ አረጋዊያን ወላጆቹን ለመንከባከብ የሚጥር ከሆነም በአላህ መንገድ ነው፡፡ ራሱን ከመጥፎ ነገር ለመታደግ ወጥቶም ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡ ለቤተሰቦቹም ፍላጎት ማሟላት የሚጥር ከሆነ በአላህ መንገድ ነው፡፡)

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የእስልምና እምነት *ሥራዎችን* እንደሁ በደፈናው እንዲናከናውን ብቻ አይደልም የሚያዘን፡፡ ይልቁንም የአላህን (ዐ.ወ.) ምንዳ በማሰብ በጥራት እንዲንፈጽመውም ይገፋፋናል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) *ሥራውን* በጥራት ለሚያከናውን ሰው ታላቅ ምንዳ እንደሚሰጠው እንድህ በማለት አብስሯል፡

{إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجْرَ مَنْ أَحْسَنَ عَمَلًا}

(እነዚያ ያመኑና መልካም *ሥራዎችንም* የሠሩ እኛ *ሥራን* ያሳመረን ሰው ምንዳ አናጠፋም፡፡) *ሥራን* በጥራት ማከናውን አላህ ከሚወዳቸው ነገሮች አንዱ መሆኑን ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት ገልጸዋል፡ (አላህ አንዳችሁ *ሥራ* በሚሠራበት ወቅት በጥራት ማከናውኑን ይውዳል)፡፡ የ*ሥራ* አመኔታ በማንኛውም ሠራተኛ፣ ተቀጣሪና ተጠያቂ ትከሻ የተጣለ ኃላፊነት ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች አላህ በቅጥታ የሚቆጣጠራቸው መሆኑን ተገንዝበው ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا}

(አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና፡፡) እንዲሁም በሌላ አንቀጽ እንድህ ይላል፡

{وَمَا تَكُونُ فِي شَأْنٍ وَمَا تَتْلُو مِنْهُ مِنْ قُرْآنٍ وَلَا تَعْمَلُونَ مِنْ عَمَلٍ إِلَّا كُنَّا عَلَيْكُمْ شُهُودًا إِذْ تُفِيضُونَ فِيهِ وَمَا يَعْزُبُ عَنْ رَبِّكَ مِنْ مِثْقَالِ ذَرَّةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَلَا أَصْغَرَ مِنْ ذَلِكَ وَلَا أَكْبَرَ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُبِينٍ}

(በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርኣን አታነብም፣ ማንኛውንም *ሥራ* አትሠሩም በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ፡፡ በምድርም ሆነ በሰማይ የብናኝ ክብደት ያክል ከጌታህ (ዕውቀት) አይርቅም፡፡ ከዚያም ያነሰ የተለቀም የለም፤ በግልጹ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ቢሆን እንጂ፡፡)

ነብያችን (ሶ.ወ.) ስለበጎ ተግባር ተጠይቀው መልስ በሰጡበት ወቅት እንድህ ብለዋል፡ (በጎ ሥራ ማለት አላህን ልክ ከፊት ለፊትህ እንደምታዮው ሆነህ መገዛትህ ነው፡፡ አንተ ባታየውም እሱ ያይሃልና)፡፡ ጌታችን ሆይ! ደጋግ ሥራዎችን እንዲንሰራ ታግዘን ዘንድ እንለምንሃለን፡፡ ግብጽና ከመጥፎ ነገር ሁሉ ጠብቅልን ሌሎችንም የዓለም ሀገራት እንደዚሁ፡፡ አሚን፡፡